አፍሪካ ቲቪ

7

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት

## ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

በቴሌግራም 6


AAcademyEthio


www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

1፡00-3:00

## ዒዳ

- ዒዳ ማለት በቋንቋ መቁጠር ማለት ሲሆን ዐደደ ከሚል ቃል የተወሰደ ነው፡፡
- በሸሪኣዊ ትርጉም ደግሞ አንዲት ሴት ለአሏህ ብላ ባሏ ሲሞት ወይም በምትለያይ ጊዜ ሌላ ባል ከማግባትዋ በፊት የምትቆይበት ወይም የምትጠብቅበት ጊዜ ዒዳ ይባላል፡፡
- ዒዳ በሸሪዓ የተደነገገ ስለሆነ እሱን መጠበቅ ግዴታ ዋጂብ ነው፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

## የዒዳ ጥበብ

- የሴት ልጅ መህፀን ከእርግዝና ንፁህ ማድረግ ይህም ከእርግዝና ነፃ መሆንዋን ለማረጋገጥ
- ለፈታው ሰው (ለመጀምሪያው ባል) ጊዜ መስጠት
- የእርግዝናን ሐቅ (መብት) ለመጠበቅ፤ የህፃን እና እናት ቀለብ እና እድገት የመሳሰሉት



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

ዒዳዎች፡- ዒዳዎች ብዙ ናቸው፡፡ እነሱም፡-

**1)** ነፍስ ጡር የሆነች ሴት እንዲሁም የፍችም ይሁን የሞት ዒዳዋ ፅንሷን መውለዷ ብቻ ነው፡፡

**2)** ባሏ የሞተባት ሴት ዒዳዋ አራት ወር ከአሥር ቀን መጠበቅ ነው፡፡

**3)** የወር አበባ የምታይ ሁና የተፈታች ሴት ዒዳዋ ሶስት የወር አበባን ማየት ሲሆን፡- ዒዳዋ የሚያበቃው ከሶስተኛው የወር አበባ መጠበቅ ነው፡፡ በአስመላሽ ፍች ዒዳ ስር ያለች ሴት ሁሉ ከባሏ ጋር መኖር ግዴታዋ ነው፡፡ ሲኖሩም ከእሷ ጋር መቀመጥም ሆነ ከእሷ ጋር ብቻቸውን መሆንም እንኳን ይችላሉ፡፡ መልሼሻለሁ በማለት ወይም የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመፈፀም ብቻ የተፈታች ሴት ወደ ሚስትነት ትመለሳለች፡፡

በዚህ ላይ የሴትዮዋ መስማማት አያስፈልግም (ግዴታ) አይደለም፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

- ከዒዳ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ሸሪዓዊ ድንጋጌዎች
- 1) የፍቺ ዒዳ፡- ከ3 ወር አባባ እስከጸዳ ባሏ ላይ በባሏ ቤት ማስቀመጥ ሸሪዓው ያስገድደዋል፤ አሏህም በቁርዓን አዝዘዋል፤ ሊቀልባት እና ሊያለብሳት ይህም ሸሪአው የሚከለክለው ነገር እስካልተፈጠረ ድረስ፤
- እሷም ከቤቱ መውጣት እና ከሱ መነጠል አይፈቀድላትም
- 2) በቋሚ መልኩ የሚያሰናብታት (መመለስ የማይችል ፍቺ) ከሆነ
- እርጉዝ ከሆነች፡-መኖሪያ ቤት እና ቀለብ ሊያደርግላት ሸሪዓው ያስገድደዋል፤
- እርጉዝ ካልሆነች፡- ለእርጉዝ የሚሆነው ሁሉ ይሆናል ከቀለብ ውጪ፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

አፍሪካ አካዳሚ

- 3) አንዲት ባሏ የሞተባት ሴት ደግሞ ባሏ የሞተባት ቤት ውስጥ ዒዳዋን 4 ወር ከ10 ቀናት መቁጠር እና እዚያው መኖር አለባት፡፡ ችግር እስካልሆነም ድረስ ልትንቀሳቀስ አይፈቀድላትም፡፡
- ባሏ የሞተባት ሴት በዒድ-ዳ ጊዜዋ ላይ (አራት ወር ከአስር ቀን) እያለች ለጌጥ የሚሆኑ አልባሳትን ትከለከላለች። ያለምክንያት ከቤት መውጣትም ትከለከላለች። ነገርግን የተለየ ጌጥነት የሌለውን ጥሩ ልብስ ግን መልበስ ትችላለች።

የአካሏን ንፅህናም ትጠብቃለች። ፀጉሯን ልታፀዳና ልታበጃጅ፣ ጥፍሮቿን ልትቆርጥ፣ ከሰዎች ጋር ልታወራ፣ አስፈላጊ ከሆነም ወንዶችን ልታነጋገር ትችላለች።

እነዚህ ነገሮች ብዙዎች የሚከለከሉ ናቸው ብለው የሚያስቧቸው ናቸው።